የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሠላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ መጋቢት ፲ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 33
ADDIS ABABA, 19th March, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፱/፪ሺ፲፯

የሕግ እና ፍትሕ ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ……...................................................ገጽ ፲፰ሺ፷፭

**Content**

Proclamation No. 1369/2025

Law and Justice Institute Establishment Proclamation ………………......Page 18065

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፱/፪ሺ፲፯

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕግና ፍትሕ ኢንስቲትዩትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የፌደራል የሕግና ፍትሕ ኢንስቲትዩት የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ለዳኝነት እና ለፍትሕ አካላት እንደመሆኑ መጠን ተጠሪነቱን ለዳኝነት አካሉ እንዲሆን በማድረግ ሥራውን በነጻነት እና በገለልተኝነት እንዲያከናውን ጥራት ያለው እና ቀልጣፋ የሕግ ጥናት እና ምርምር እንዲሁም የሥልጠና አገልግሎት መስጠት እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ተጠሪነቱ ለዳኝነት አካሉ የሆነ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ስራውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችል የሰው ኃይል እና የአሰራር አደረጃጀት ያለው የፍትሕ እና ሕግ ተቋም በማቋቋም በእውቀቱ፣ በክህሎቱ፣ በአመለካከቱ፣ እንዲሁም በሥነ-ምግባሩ ብቁ የሆነና የተሟላ ስብዕና ያለው የዳኝነት እና የፍትህ አካላት አመራር እና ባለሙያ ማፍራት ለፍትሕ ስርዓቱ ውጤታማነት እጅግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## PROCLAMATION No 1369/2025

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLSIHEMENT OF THE F.D.R. E. LAW AND JUSTICE INSTITUTE

**WHEREAS**, it is found necessary to enable the Federal Law and Justice Institute to carry out its activities independently and impartially and deliver quality and efficient legal research as well as training services, by making it accountable to the judiciary, as it delivers services for the judiciary and other justice sector organs;

**WHEREAS**, it is found highly necessary for effectiveness of the justice system to produce judicial and justice organs' professionals with knowledge, skill, attitude as well as ethics by establishing an institution of law and justice, accountable to the judiciary, being equipped with modern technology, human resource and system of structure that enables to properly carry out its activities;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ሕጎችን ከወቅታዊ የዓለም እና የሀገሪቱ የዕድገት ደረጃ ጋር እንደዚሁም ሃገራችን ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ ለማድረግ እንዲሁም የዳኝነት፣ የፍትሕ አካላትና ሌሎች ከፍትሕና ሕግ ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላትን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ ለማድረግ ጥናትና ምርምሮችን ማከናወን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሀገሪቱ የዳኝነት እና ፍትሕ ዘርፍ የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት እያሳካ ስለመሆን አለመሆኑ የሚያሳይ አስተማማኝና የተሟላ የሕግና ፍትሕ መረጃ ለመሰብሰብ እና ለማደራጀት የሚችል በቂ የሰው ኃይል እና አግባብነት ያለው የአሰራር እና አደረጃጀት ሥርዓት ያለው ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዳኝነት፣ የፍትሕ አካላት እና የሕግ ትምህርት ቤቶች የሚቀናጁበትን እንዲሁም በፍትሕ ሥርዓቱና በሕግ ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ የሚደረጉ የማሻሻያ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ ለመምራትና ለማስፈጸም የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሕግ እና ፍትሕ ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፱/፪ሺ፲፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**WHEREAS**, it is found necessary to carry out researches, with a view to harmonize laws with contemporary development level of the world and the country as well as international treaties ratified by our country and to make efficient, effective and accessible the judiciary, justice organs and other entities having a relationship with law and justice activity;

WHEREAS, it is found necessary to establish an institution with sufficient human resource and appropriate working system and structure capable to gather and organize reliable and comprehensive law and justice data indicating whether the justice sector of the country is effectively achieving the mission assigned to it;

**WHEREAS**, it is necessary to put in place a system that enables coordinating the judiciary, justice organs and law schools as well as directing and executing in coordinated manner the reform works implemented in the justice system and law schools;

**NOW THERE FORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## SECTION ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short title**

This proclamation may be cited as the "Law and Justice Institute Establishment Proclamation No. 1369 /2025".

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ዳኝነት አካላት"** ማለት የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ሲሆኑ፣ እንደ አግባብነቱ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው በፌደራልና በክልል የሚገኙ ሌሎች አካላትን ይጨምራል፤

፪/ **"የፍትሕ አካላት"** ማለት የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የፌደራል ማረሚያ ቤት፣ የፌደራል ጠበቆች ማሕበር እና የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤትን የሚያካትት ሲሆን በክልሎች የሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማትን ወይም አደረጃጀቶችን ይጨምራል፤

፫/ **"የዳኝነት አካላት ባለሙያዎች"** ማለት መደበኛ ዳኞችን፣ ጊዜያዊ ዳኞችን፣ ረዳት ዳኞችን፣ ሬጅስትራሮችን፣ የሚያጠቃልል ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ባለሙያዎችን ይጨምራል፤

፬/ **"የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች"** ማለት ዐቃቤያነ ሕግ፣ የፖሊስ እና ማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላትን፣ ጠበቆችን እና ተከላካይ ጠበቆችን የሚያጠቃልል ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ከፍትሕ እና ሕግ ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት ባለሙያዎችን ይጨምራል፤

፭/ **"የፍትሕ መረጃ ትንተና"** ማለት ከዳኝነት አካል እና ከፍትሕ እና ሕግ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በማደራጀት እና በመተንተን የሀገሪቱን የዳኝነት የፍትሕ ሥርዓት ትክክለኛና የተሟላ ገጽታ የሚያሳይ አስተማማኝ መረጃ የማቅረብ ሂደት ነው፤

## 2. Definition

In this proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "**Judicial Organs**" means Federal and State courts and it may, where appropriate, include institutions empowered with judicial functions in accordance with law at the Federal as well as State level;

2/ "**Justice Organs**" means Ministry of Justice, Federal Police Commission, Federal Prison Administration, Federal Bar Association, Federal Public Defenders' Office and include such similar institutions established at State level;

3/ "**Judicial Organs Professionals**" include regular judges, Ad-Hoc judges, Assistant Judges, Registrars, and where appropriate, it also include professionals of institutions empowered with judicial functions;

4/ "**Justice Organs Professionals**" means public prosecutors, members of the police commission and prison administration, defense attorneys and public defenders and include professionals whose responsibilities are related with justice and law;

5/ "**Justice Data Analysis**" means a process of a systematic organization and analysis of Law and Justice related data and presentation of reliable information that demonstrate the accurate and complete picture of the country's judicial organs and justice system;

፮/ **"የሥራ ላይ ሥልጠና"** ማለት የዳኝነት አካላት ወይም የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች እና አመራሮች በመደበኛ ሥራቸው ላይ ሆነው የሚወስዱት የግዴታ ሥልጠና ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ከሥራቸው እና ከሥራ አካባቢያቸው ባህርይ ጋር የተያያዙ ሥልጠናዎችንም ይጨምራል፤

፯/ **"ቅድመ ሥራ ሥልጠና"** ማለት ጀማሪ ወይም አዳዲስ የሕግ ባለሙያዎች የዳኝነት ወይም የፍትሕ አካላትን ከመቀላቀላቸው በፊት የግዴታ የሚወስዱት ተግባር ተኮር ሥልጠና ነው፤

፰/ **"ልዩ ሥልጠና"** ማለት ከዳኝነት፣ ከፍትሕ እና ከሕግ አውጪ አካላት ውጪ የሆኑ ሌሎች አካላት ከሕግ እና ፍትሕ ጋር የተያያዘ ሥልጠና ወጪውን በመሸፈን የሚወስዱት ሥልጠና ነው፤

፱/ **"የሥራ ማስተዋወቂያ ሥልጠና"** ማለት የዳኝነት እና የፍትሕ አካላትን በቅጥር ወይም በሹመት የሚቀላቀሉ ባለሙያዎችን ወይም የሥራ ኃላፊዎች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ስለተቋሙና በተቋሙ ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎችን ለማስተዋወቅ የሚሰጥ ሥልጠና ነው፤

፲/ **"የአመራር ሥልጠና"** ማለት ለዳኝነት እና ለፍትሕ አካላት በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮች የሚሰጥ ሥልጠና ነው፤

፲፩/ "**ቦርድ**" ማለት ኢንስቲትዩቱን በበላይነት የሚመራ የሥራ አመራር ቦርድ ነው፤

፲፪/ "**ክልል**" ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

6/ "**On Job/In Service Training**" means a mandatory training that judicial and justice organs professionals and leaders should take while they are on duty and includes other trainings related to their duties and nature of their functions;

7/ "**Pre-Service Training**" means a practical/practice oriented mandatory training provided for junior or fresh legal professionals before joining the judicial or justice organs;

8 "**Special Training**" means a training provided on law and justice related matters to other bodies, which are not part of the judiciary, justice organs and law makers, through covering their cost of training;

9/ "**Induction Training**" means an induction or orientation training to new entrant employees or officials joining judicial or justice organs for the purpose of introducing them about the institution to which they are joining;

10/ "**Leadership Training**" means a training provided for middle and upper level managerial staffs of the judicial and justice organs serving at different levels;

11/ "**Board"** means the highest leadership of the Institute;

12/ "**Region**" means any region specified in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administration;

፲፫/ “**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው፤

፲፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ አነጋገር ለሴት ጾታም ያገለግላል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>መቋቋም፣ ሥልጣን እና ተግባራት</u>**

**፫. <u>መቋቋም</u>**

፩/ የፌደራል የሕግ እና ፍትሕ ኢንስቲትዩት ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩት” እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

**፬. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በቦርዱ ውሳኔ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶችን በአገሪቱ ሌሎች ቦታዎች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**፭. <u>ዓላማ</u>**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የአገሪቱን የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ተደራሽ፣ ገለልተኛ እና የሕዝብ አመኔታ ያተረፉ እንዲሆኑ የሚያግዙ በቴክኖሎጂ የተደገፉ፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን ያገናዘቡ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፤

፪/ የዳኝነትና የፍትሕ አካላት አመራሮችን እና ባለሙያዎችን በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት እና በሥነ ምግባር በማነጽ የፍትሕ ዘርፉ ከፍተኛ ሙያዊ ብቃት እና ሥነ-ምግባር ባላቸው አመራሮች እና ባለሙያዎች የተገነባ እንዲሆን ማስቻል፤

13/ “**Person**” means any natural person or juridical organ;

14 / Any expression in the masculine gender shall apply to the feminine.

**<u>SECTION TWO</u>**

**<u>ESTABLISHMENT, POWERS AND RESPONSIBILITIES</u>**

**3. <u>Establishment</u>**

1/ The Federal Law and Justice institute here in after referred to as the “Institute” is here by re-established as an autonomous Federal Government Office having its own legal personality;

2/ The institute shall be accountable to the Federal Supreme Court.

**4. <u>Head Office</u>**

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and when appropriate, it may also have branch offices at any part of the country by the decision of the Board.

**5. <u>Objectives</u>**

The institute shall have the following objectives:

1/ To undertake researches and studies, assisted with technology by taking into account international agreements and best practices, that enable the judicial and justice organs of the country be efficient, effective, accessible, impartial, and trustworthy by the public;

2/ Building the judicial and justice sector with the highest professional competence and integrity through enhancing the knowledge, skill, attitude and ethical standards of the leadership and professionals of the judicial and justice organs;

፫/ በሀገሪቱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት የሥልጠና እና የጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል፤

፬/ የሀገሪቱን የፍትሕ ሥርዓት ትክክለኛና የተሟላ ገጽታ የሚያሳይ የፍትሕና የሕግ መረጃ ለመሰብሰብ እና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፡፡

## ፮ <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣን እና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የሕግ ማሻሻያና ማሚያ የጥናትና ምርምር መርሐ-ግብር በመንደፍ፡-

ሀ) በየዘርፉ ያሉ ነባር ሕጎችን ለማሻሻል እና አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት፤

ለ) የሕግ ትምህርት እና ሥልጠናን ለማጠናከር፤

ሐ) የዳኝነት እና የፍትሕ አካላትን የሰው ሀብት ብቃት ለማሳደግ፣ አደረጃጀታቸውን እና አሰራራቸውን ለማሻሻል፤ እና

መ) ከሕግ ብዝሐነት ጋር የተያያዙ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች እና ሌሎች ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች ከመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፤

የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፡፡

፪/ የፍትሕ መረጃ ትንተና በማከናወን የሀገሪቱ የፍትሕ ዘርፍ ተልዕኮውን በአግባቡ እያሳካ መሆኑን ለማወቅ የሚያስችል አስተማማኝና የተሟላ መረጃ ያቀርባል፤

3/ Serving as a center of excellence of the country through utilizing modern technology in training, and research and studies of the judicial and justice organs;

4/ Establishing a system to gathering and making accessible a comprehensive and adequate justice and law information about the country's justice system.

## 6. <u>Powers and Duties of the Institute</u>

The institute shall have the following powers and duties:

1/ Design research and studies on law revision and amendment, and conduct research and studies to:

a) Revise existing laws and initiate new ones;

b) Strengthen legal education and training;

c) Enhance the human resource capacities, and improve organization and performance of the judicial and justice organs;

d) Facilitate integration and collaboration of various dispute resolution mechanisms and traditional justice systems, related to legal pluralism, with the formal justice system of the country;

2/ Carryout justice and law information analysis and make accessible a reliable and comprehensive information to realize whether the justice sector is in a position of achieving its mission;

፫/ የፍትሕ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚረዱ የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት የጋራ ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፣ ያስተባብራል፣ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል አስፈላጊ ሲሆንም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፬/ ከክልል የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ማዕከላት ጋር በመተባበር የአጭር እና ረጅም ጊዜ ሥልጠና ካሪኩለም ያዘጋጃል፤

፭/ የፌደራል የዳኝነት እና የፍትሕ አካላትን ለሚቀላቀሉ እንዲሁም ከክልሎች ጋር በሚኖረው ትብብር መሠረት የራሳቸው ሥልጠና ማዕከል ለሌላቸው ክልሎች የዳኝነትና የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች እና ሌሎች ከዳኝነት እና ሕግ ማስከበር ጋር ተያያዥነት ያለው ሥራ ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሥራ ማስተዋወቂያ እና የቅድመ ሥራ ሥልጠና ይሰጣል፤

፮/ ለዳኝነት እና የፍትሕ አካላት አመራሮች የሚሆን የሥልጠና መርሐ-ግብር በማዘጋጀት ሥልጠና ይሰጣል፤

፯/ በፌደራል እና በክልሎች መካከል በሚኖር ትብብር መሠረት በክልል የሥልጠና ማዕከላት ለሚሠሩ አሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣ ብቃታቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፰/ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ለማጎልበት የሚረዱ በተለይም በቴክኖሎጂ የተደገፉ አሠራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ምርምሮችን በማካሄድ ወይም እንዲካሄዱ በማድረግ የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፤

3/ Design, coordinate, monitor, evaluate, and where necessary take corrective measures on common reform projects of the judicial and justice organs that help to improve the justice system;

4/ Prepare a curriculum for short and long term trainings in consultation with Regional States Legal Research and Training Institutes;

5/ Provide induction, pre-service and on-job trainings to those joining the Federal Judicial and Justice Institutions and, based on the cooperation with Regional States that do not have their own training center, to the judicial and justice organs professionals and other professionals carrying out quasi-judicial and other law enforcement duties;

6/ Design a training program and provide trainings for judicial and justice organs leadership;

7/ Based on federal-regional cooperation arrangement, provide trainings for trainers working at Regional States Training Centers and design a system to certify their competence;

8/ Carry out or cause to be carried out researches aiming at improving technology assisted case flow management system of courts and forward recommendations thereto;

፱/ ከዳኝነት እና የፍትሕ አካላት አመራር እና ከፍትሕ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ሀገር አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ዓውድ ጥናቶች ወይም የጥናት እና ምርምር ጉባኤዎችንና መድረኮችን እንዲሁም ትምህርታዊ ገለጻዎች ያካሂዳል ይሳተፋል፤

፲/ የፍትሕ አስተዳደርን ለማገዝ ጥናትና ምርምርን ከሚያካሂዱ የምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፲፩/ የጥናትና ምርምር ውጤቶቹን ያሳትማል፣ ያሰራጫል፣ የሥልጠና ጽሁፎችን ያዘጋጃል፣ ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፤

፲፪/ ሕግ እና ፍትሕ ነክ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና በማደራጀት የፍትሕ መረጃ ማዕከል ያቋቁማል፣ ተደራሽ ያደረጋል፤

፲፫/ ከሕግ ትምህርት ቤቶች እና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ከፍትሕና ሕግ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የጥናትና ምርምር ጉባኤዎችንና መድረኮችን እንዲሁም ትምህርታዊ ገለጻዎችን ያዘጋጃል፤

፲፬/ ከሕግ ትምህርት ቤቶች ጋር በመቀናጀት የሕግ ተማሪዎች ዕንሰ ሀሳባዊ ትምህርትን ከተግባር ጋር ለማዛመድ የሚያስችላቸውን ምስለ ፍርድ ቤትን ጨምሮ ዕውቀት የሚገበዩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፭/ ለዓላማው መሳካት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከሚችሉ የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ አገር የጥናት እና ምርምር፣ የትምህርት፣ ሥልጠናና ሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፣ በጋራ ይሰራል፤

9/ Conduct national, regional and international research conferences, symposiums, workshops and educational briefings in relation to the leadership and over all judicial and justice administration;

10/ Work in collaboration with research institutions, Universities and other entities with the view of assisting the justice administration;

11/ Publish and disseminate research outputs, prepare, collect and distribute training materials;

12/ Collect and organize Law and Justice related information and establish justice and law information data center and make accessible;

13/ Arrange research conferences, symposiu ms and workshops in relation to justice and law in collaboration with Law schools and other appropriate entities;

14/ In collaboration with law schools, design a system of enabling law students to acquire knowledge about the law in theory and its practical application by arranging moot court competitions and other means;

15/ Establish a relationship and work in collaboration with international and local research, Training, educational and other institutions that can contribute for the achievement of its goals;

፲፮/ ከዓላማው ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ለሌሎች አካላት ለሚሰጠው የጥናትና ምርምር፣ የማማከር፣ ሥልጠና፣ የፈተና አገልግሎት በቦርዱ በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ክፍያ ያስከፍላል፤

፲፯/ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## አደረጃጀት እና አሰራር

### ፯. የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት

ኢንስቲትዩቱ ፡-

፩/ ቦርድ፤

፪/ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፤

፫/ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፬/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

### ፰. የቦርድ አባላት

ቦርዱ የሚከተሉት ሰባት አባላት ይኖሩታል፦

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት------------------------------------------------ ሰብሳቢ፤

፪/ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ ሚኒስትር ----------------------------------------------------ምክትል ሰብሳቢ፤

፫/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ----------------------------------------------------------አባል፤

፬/ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ----------------------------------------------------አባል፤

፭/ የፌደራል ጠበቆች ማህበር ፕሬዚደንት ------------------------------------------------------አባል፤

16/ Charge fees, based on the directive issued by the Board, for the service it provides in relation to research and studies, consultancy, training and exam administration on topics having relevance to its objectives;

17/ Perform other activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

## SECTION THREE
## STRUCTURE AND FUNCTION

### 7. Structure of the Institute

The Institute shall have:

1/ A Board;

2/ A Director General appointed by the Prime Minister upon the nomination of the President of the Federal Supreme Court;

3/ Deputy Director Generals, as may be necessary;

4/ The necessary expert professionals and staffs.

### 8. Members of the Board

The board shall have the following seven members:

1/ The President of the Federal Supreme Court……………………..……Chairperson;

2/ The Minister of the Ministry of Justice ...…………………......Deputy Chairperson;

3/ A Member of the House of Peoples' Representatives………………...Member;

4/ A State Minister of the Ministry of Education………………………Member;

5/ President of the Federal Advocates' Association ..........…........…….. Member;

፮/ የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ----------------------------------------------አባል፤

፯/ የሕግ ትምህት ቤቶች ማህበር ሰብሳቢ ----------------------------------------------አባል፤

፰/ የኢንስቲቲዩቱ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ያለ ድምጽ ይሳታፋል።

**፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱን ዕቅድ፣ የሥራ መርሐ-ግብሮችን፣ ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ ይገመግማል፣ ያፀድቃል፣ አስፈላጊ በጀት እንዲፈቀድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብ ይወስናል፣ እንዲፈቀድም ክትትል ያደርጋል፤

፫/ ምርምርንና ሥልጠናን አስመልክቶ የሚቀርቡ የፖሊሲ ጉዳዮችን ይገመግማል፣ ይወስናል፤

፬/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡለትን የሥልጠና ካሪኩለም፣ የምርምር መርሐ ግብሮችን እና የመፍትሔ ወይም የውሳኔ ሀሳቦችን ያፀድቃል፤

፭/ የኢንስቲትዩቱን መርሐ ግብሮችን፣ ፕሮጀክቶችን ይገመግማል ያፀድቃል፤

፮/ የኢንስቲትዩቱን ዓላማ ለማስፈጸም የሚረዱ ድጋፎችንና ስጦታዎችን በሚመለከት አጠቃላይ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፯/ የኢንስቲትዩቱን ድርጅታዊ መዋቅር እና የተለያዩ የውስጥ ሥራ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤

6/ Head of the Public Defenders' Office ……………………….…...… Member;

7/ Chairperson of the Ethiopian Law Schools Association…………..….. Member;

8/ Director General of the Institute Non-voting member and Secretary of the board

**9. Powers and Duties of the Board**

The board shall have the following powers and duties:

1/ Lead the activities of the institute;

2/ Review and approve the institute's plans, working schedules and annual reports and decides on the proposed annual budget of the institute to be submitted to the House of Peoples Representatives and follow up its approval;

3/ Review and decide on policy matters in relation to research and training;

4/ Approve training curriculums, research schedules and recommendations and submitted to it by the Director General;

5/ Review and approve programs and projects of the Institute;

6/ Provide general directions on matters pertaining to assistances and donations for the realization of the objectives of the Institute;

7/ Approve the organizational structure and issue various internal working Directives of the Institute;

፰/ የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ፈጻሚ ሙያተኞች፣ አሰልጣኞች እና ተመራማሪዎች በዳኞችና በዐቃቤያን ሕግ ደምወዝና ጥቅማ ጥቅም እስኬል መርህ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፤

፱/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ በተደነገገው መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች እንዲቋቋሙ ይወስናል፤

፲/ ሌሎች በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡ ጉዳዮችን መርምሮ ይወስናል፡፡

**፲. <u>የቦርዱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት</u>**

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢ የቦርዱን ስብሰባ ይመራል፣ ሰብሳቢው በማይገኝበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ስብሰባውን ይመራል።

፪/ ቦርዱ ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ አሳሳቢነት የቦርድ ሰብሳቢ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

፫/ የቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፬/ ማናቸውም ውሳኔ የሚተላለፈው ስብሰባው ላይ ከተገኙ አባላት ከግማሽ በላይ ድምፅ ሲደገፍ ነው፣ ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

8/ Cause the salary scale and benefit packages of the core professionals, trainers and researchers of the Institute be executed based on the principles applicable to the salary and benefit packages of the judiciary and public prosecutors;

9/ In accordance with Article 4 of this Proclamation, decide on the opening of branch offices of the Institute in any part of the country as may be appropriate;

10) Decide on other matters submitted to it by the Director General.

**10. <u>Meeting Procedure of the Board</u>**

1/ The chairperson shall preside over the meeting of the Board; in his absence, the Deputy Chair person shall preside the meeting.

2/ The Board shall hold at least One session quarterly and when necessary urgent meetings deemed may be called by the chair person upon the request of the Director General.

3/ There shall be quorum when more than half of the members of the Board are in attendance.

4/ Decision of the board shall be made by a simple majority, but whenever there is a tie, the chairperson shall have a casting vote.

5/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board my issue a Directive of its meeting procedure.

**፲፩. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባራት</u>**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ላይ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣን እና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) ዕቅድ፣ መርሐ-ግብር እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) የሥልጠና ካሪኩሊም፣ የምርምር መርሐ-ግብሮችን እና የመፍትሔ ወይም ውሳኔ ሀሳቦችን ለቦርድ አቅርቦ ያስፀድቃል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ መርሐ-ግብር መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) የኢንስቲትዩቱ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በሚመለከት ከፌደራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሰራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በሚፈፀምበት ሕግ መሠረት ያስፈፅማል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ሸ) ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

**11.<u>Powers and Duties of the Director General</u>**

1/ The Director General shall be the Chief Executive Officer of the Institute and direct and manage the activities of the Institute.

2/ Without prejudice of the generality of the provision of Sub Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Execute the powers and duties of the Institute stipulated under Article 6 of this Proclamation;

b) Prepare and submit the work plan and budget of the Institute to the Board; and implement same upon approval;

c) Prepare and submit to the Board for approval the training curriculum, research programs and schedules and recommendations;

d) Effect expenditure in accordance with the approved budget and work plan of the Institute;

e) Execute the salary and benefit package of the administrative support staff of the Institute in accordance with the law of the salary and benefit package of the Federal courts’ administrative support staff ;

f) Represent the Institute in all dealings with third parties;

g) Prepare and submit to the Board the performance and financial report of the Institute;

h) Execute other related tasks assigned to him by the Board.

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣን እና ተግባራቱ በከፊል ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

3/ The Director General may, to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute, delegate part of his power and duties to the Deputy Director Generals and other officials and employees of the Institute.

**፲፪. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣን እና ተግባራት</u>**

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

፩/ በኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት የሚመደቡበትን የሥራ ዘርፍ ይመራሉ፣ ያስተዳድራሉ፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጧቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፤

፫/ ተለይቶ ካልተወከለ በስተቀር ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይም የኢንስቲትዩቱ ዋና ዓላማ ስኬት የበለጠ ቅርበት ያለውና ሰፊ የእለት ተዕለት ተግባር የሚመራው ምክትል ዋና ዳሬክተር ተክቶት ይሠራል፡፡

**12. <u>Powers and Duties of Deputy Director Generals</u>**

The Deputy Director Generals of the Institute shall:

1/ Direct and administer the sector assigned to them in accordance with the institute's organizational structure;

2/ Perform tasks assigned to them by the Director General;

3/ Unless the Director General delegates otherwise, the senior Deputy Director General having more close ties with the day-to-day activities of the Institute to meet its objectives shall act on behalf of the Director General in his absence.

**፲፫. <u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

፩/ በመንግስት የሚመደብ በጀት፤

፪/ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ከሰበሰበው የውስጥ ገቢ፤

፫/ ከዳኝነት እና ፍትሕ ዘርፉ ጋር የሚዛመድ ፕሮግራም ካላቸው ለጋሽ አካላት የተሰጠ ድጋፍ፡፡

**13. <u>Budget</u>**

The budget of the Institute shall be drawn from the following sources:

1/ Budget allocated by the government;

2/ Internal incomes collected as charges in accordance with the Directive issued by the Board;

3/ Grants and funds donated by partners having programs and projects in relation to Judiciary and Justice sectors.

**፲፬. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በፌደራል ዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፭. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

የፌደራል ፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት መብት እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ወደ ኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡፡

**፲፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩትን፣ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከልን እንዲሁም የፌደራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት ሥልጣን እና ተግባር ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎች እና የተዘረጉ አሰራሮች በሌሎች መመሪያዎች እና አሰራሮች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**፲፯. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ የፌደራል ፍትሕ እና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፩/፪ሺ፲ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/ ፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፺፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሽሯል፤ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፫/ ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**14. Books of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of account.

2/ The Institute's books of account and financial documents shall be audited annually by the Federal Auditor Generalor an auditor to be assigned by the Federal Auditor General.

## SECTION FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**15. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Federal Justice and Law institute is hereby transferred to the Institute.

**16. Transitory Provisions**

Directives issued and procedures set in order to execute the powers and duties of the Justice and Legal System Research Institute, the Justice Organs Professionals Training Center and the Justice and Law Institute shall remain in force until replaced by new Directives and Procedures.

**17. Repealed Laws**

1/ The Federal Justice and Law Research and Training Institute establishment Proclamation no. 1071/2018 is hereby repealed.

2/ Article 98 Sub-Article (3) of Proclamation No.1263/2021 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs is hereby repealed; and therefore the previous Sub-Articles (4) and (5) are hereby re arranged as Sub-Articles (3)and(4).

3/ No laws, regulations, directives or practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, have effect with respect to matters provided for by this Proclamation.

**፲፰. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቦርዱ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፲ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**18. Power to issue Regulations and Directives**

1/ The House of Peoples' Representatives may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Board shall have the power to issue directives for the implementation of this Proclamation and Regulations to be issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**19. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 19th Day of March, 2025**

**TAYE ATSKE-SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**